**ስርዓት**
ፌርቪው የጤና አገልግሎቶች (Fairview Health Services)

**ፖሊሲ**

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ

*የታተሙ ቅጂዎች ለዋቢነት ብቻ የሚሆኑ ናቸው። በጣም ለቅርብ ጊዜው ስሪት እባክዎን የኤሌክትሮኒክ ቅጂውን ይመልከቱ።*

**ዓላማ፡-**
የፌርቪው የጤና አገልግሎቶች (Fairview Health Services) እና HealthEast (አንድ ላይ፣ "Fairview") በማህበረሰባችን ውስጥ ላሉ ታካሚዎች የመክፈል አቅማቸው ምንም ይሁን ምን ጥራት ያለው የጤና እንክብካቤ የማቅረብ ረጅም ታሪክ አለው። አንዳንድ ሕመምተኞች የጤና መድን ሽፋን ስላልነበራቸው ወይም የጤና እንክብካቤ ወጭዎቻቸው ከመክፈል አቅማቸው ስለሚበልጡ ላገኙዋቸው በሕክምና አስፈላጊ የሆኑ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል መክፈል እንደማይችሉ Fairview ይገነዘባል። ለችግረኞች ተገቢውን የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ወይም ሌላ የገንዘብ ድጋፍ ለመስጠት፣ Fairview ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ የታካሚ ብቁነትን ለመገምገም የሚያስችል ሂደት አለው።

**የፖሊሲ መግለጫ፡-** Fairview የማህበረሰቡን ጤና ለማሻሻል ቁርጠኛ ነው። ይህ ፖሊሲ የ Fairview ን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ የተለያዩ ክፍሎችን ይመለከታል።

**ትርጓሜዎች፡-**

**አስፈላጊ ሕክምና**
ከሕክምና አንፃር አስፈላጊ የሆነ እንክብካቤ ማለት፣ በ Fairview ዕውቅና በተሰጠው የሕክምና ሐኪም/የሕክምና ባለሙያ አመለካከት እና በመደበኛ የእንክብካቤ ደረጃ መሰረት የሚከተሉትን ለማድረግ አሳማኝ በሆነ መልኩ የሚያስፈልግ የሕክምና ክትትል ነው፡-

- የሕመም፣ የጤና ሁኔታ ወይም የአካል ጉዳት እንዳይከሰት ወይም እንዳይባባስ ለመከላከል፤
- ምርመራ ለማካሄድ፤
- ለአካላዊ፣ ለባህሪያዊ እና/ወይም ለአእምሮአዊ የጤና እክሎች የማስታገሻ፣ ፈዋሽ ወይም የማገገሚያ ሕክምና ለመስጠት፤ እና/ወይም
- የግለሰቡን የአሰራር ችሎታ እና በግለሰቡ የእድሜ ደረጃ ላይ ላሉ ሰዎች ተገቢ የሆኑ የአሰራር ችሎታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን በማከናወን ረገድ ግለሰቡ የአሠራር አቅም እንዲያገለብት ወይም ይህንን ችሎታ ጠብቆ ማቆየት እንዲችል ለማገዝ።
- በሕክምና አስፈላጊ አገልግሎቶች በፌዴራል የማኅበራዊ ዋስትና ሕግ ርዕስ XIX በተደነገገው መሠረት ተኝቶ የሚታከም እና የተመላላሽ ህመምተኛ ሕክምና አገልግሎቶችን እንዲሁም በፌዴራል የማኅበራዊ ዋስትና ሕግ ርዕስ XVIII መሠረት የሚሸፈን እና በሕክምና አስፈላጊ ነው ተብሎ የሚታሰብ ማንኛውንም ተኝቶ የሚታከም ሕመምተኛ ወይም የተመላላሽ የሆስፒታል አገልግሎትን ያካትታሉ። በተጨማሪም፣ ሆስፒታሉ ካፒታል ወይም ትርፍ ጥቅም በሚያስገኝበት አጋርነት ወይም በ LLC (ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት) በሆስፒታሉ ተቋም ውስጥ የሚሰጥ እንክብካቤ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ነው። አገልግሎቶቹ በሚሰጡበት ጊዜ በአብዛኛው ተቀባይነት ባላቸው ብሔራዊ የሕክምና ደረጃዎች መሠረት አገልግሎቶች መከናወን አለባቸው። እያንዳንዱ አገልግሎት ዓላማውን በተገቢ ለማሳካት በመጠን፣ በቆይታ እና በስፋት በቂ መሆን አለበት።
- በሕክምና አስፈላጊ አገልግሎቶች በሙከራ ደረጃ የሚሰጡ ወይም በባህሪያቸው ውበት-ነክ የሆኑ አገልግሎቶችን አያካትቱም።
- በጣም አስፈላጊ የሆኑ የሕክምና ዓይነቶችን የሚደግፉ ሌሎች ሁኔታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-
    - ይህ የተለየ ሁኔታ ያላቸው ታካሚዎች ከተጠየቀው ህክምና ተጠቃሚ እንደሚሆኑ የሚያሳይ ከፍተኛ ጥራት ያለው ሳይንሳዊ ማስረጃ፤
    - የጥቅሙ ዓይነት ክሊኒካዊ አስፈላጊነት ያለው ሲሆን፤ እና/ወይም
    - አነስተኛ ዋጋ ያላቸው አማራጭ ሕክምናዎች እና የአሰጣት መንገዶች ከግምት ውስጥ ገብተው ውድቅ ሲደረጉ።

**የሙከራ ሕክምናዎች**
በሙከራ ደረጃ የሚሰጡ ሕክምናዎች የጤናውን ሁኔታ በምርመራ ለይቶ በማወቅ፣ በመከላከል እና በማከም ረገድ አግባብነት ባለው መስክ በሚሠሩ ባለሙያዎች በአብዛኛው አስተማማኝ እና ውጤታማ ሆነው ያልተገኙ ሕክምናዎች እና የምርመራ ሂደቶች ናቸው። አንድ

ሕክምና የሙከራ እንደሆነ በሚወሰንበት ጊዜ፣ አግባብነት ያላቸው ምክንያቶች በዚህ ባይገደቡም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፦

- ሕክምናው የክሊኒካል ጥናት ክፍል ብቻ ሆኖ መገኘቱ ወይም አለመገኘቱ፤
- በአቻ በተገመገሙ ጆርናሎች ውስጥ ያሉ አግባብነት ያላቸው ጽሁፎች ሕክምናው ላይ እየታየ ላለው የጤና ሁኔታ ተጨማሪ ጥናት እንዲደረግ ጥሪ ማቅረባቸው፤ ወይም
- ሕክምናው በተለየ የሰውነት አካል አካባቢ ላይ፣ ጉልህ በሆነ መልኩ በተለየ መንገድ እና/ወይም ለተለየ የጤና ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋል አለመዋሉ፣ ከዚያም በአጠቃላይ አግባብ ባለው መስክ [በ Fairview፣ በትዊን ሲቲ፣ ሚኒሶታ፣ ዩ.ኤስ፣ ወዘተ ውስጥ] ባሉት ሌሎች ባለሙያዎች ተቀባይነት ማግኘት አለማግኘቱ።

**ከፋይናንስ አንፃር ለመቋቋም የሚከብድ ሸክም**
አገልግሎቱን ለማቅረብ ለ Fairview ከግብር ነፃ የሆነ አካል ከፍተኛ ወጪ የሚኖርበት ሁኔታ እና ለአገልግሎቱሊኖሩ ለሚችሉ የታካሚ ፍላጎት ተቋሙ ተመሳሳይ ሁኔታ ላላቸው ሁሉም ታካሚዎች በቂ ክፍያ ሳይደረግ ተመሳሳይ አገልግሎት መስጠት እና በፋይናንስ ረገድ ብቁ ሆኖ መቀጠል በማይችልበት ክስተት።

**ቤተሰብ**
ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣ ቤተሰብ የሚባለው:

- በአገር ውስጥ ገቢ አገልግሎት (IRS) መመሪያዎች እንደተገለጸው ባል እና ሚስት እና ማንኛውም ጥገኞቻቸው።
- በ IRS መመሪያዎች እንደተገለጸው ጥገኞች ያሉት/ያሏት ግለሰብ።
- ጥገኞች የሌሉት/የሌሏት ያላገባ/ያላገባች ሰው።

ቤቱ ከአንድ በላይ ቤተሰብ የያዘ ከሆነ የድህነት መመሪያዎች ለእያንዳንዱ ቤተሰብ በተናጠል ተግባራዊ ይደረጋሉ።

**የእንክብካቤ አቅርቦት**
Fairview የመክፈል ችሎታን ከግምት ውስጥ ባላስገባ መልኩ ለድንገተኛ ጊዜ የሕክምና ሁኔታዎች የሕክምና ማጣሪያ ምርመራዎችን እና የማረጋጊያ አገልግሎቶችን ይሰጣል። (የ HealthEast ወይም የ Fairview EMTALA ፖሊሲዎችን ይመልከቱ። )

Fairview በ Fairview እውቅና ባለው ትዕዛዝ ሰጪ ሐኪም አተያይ መሰረት በሕክምና አስፈላጊ የሆኑ ድንገተኛ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ይሰጣል። እርካታቸውን ለማሳካት ድንገተኛ ያልሆኑ አገልግሎቶች ከመሰጠታቸው በፊት Fairview የክፍያ ቅድመ ዝግጅቶች መኖራቸውን ሊጠይቅ ይችላል። የክፍያ ቅድመ ዝግጅቶች በጥሬ ገንዘብ ወይም በክሬዲት ካርድ ክፍያ፣ በ Fairview ተቀባይነት ያለው የመድን ዓይነት፣ የመድን አልባ የዋጋ ቅናሽ፣ እንዲሁም በሚቻልበት ጊዜ በ Fairview የፀደቀ የገንዘብ ድጋፍ (ቅናሽ ወይም ነፃ እንክብካቤን) ሊያካትቱ ይችላሉ። የተመረጡ አገልግሎቶች ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ላይሆኑ ይችላሉ። Fairview አስቸኳይ ባልሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ፣ እጅግ በጣም ተገቢውን የህክምና መንገድ ከህክምና እና ከሥነ ምግባራዊ እይታ አንጻር ለመምረጥ እያንዳንዱን ጉዳዮች ወይም የተወሰኑ አገልግሎቶችን የመገምገም መብቱ የተጠበቀ ነው።

**የመድን ዋስትና የሌለው ቅናሽ (የ Fairview ሆስፒታሎች)**
Fairview እና HealthEast ከጠቅላይ አቃቤ ሕግ ጋር ባደረጉት ከጁን 2017 እስከ ጁን 2022 ድረስ ተግባራዊ በሚሆኑ ስምምነቶች (በጥቅሉ “ስምምነቶች”) በገለጹት መሠረት የመድን ዋስትና የሌላቸው ህክምናዎች የሚያገኙ የሆስፒታል ሕመምተኞች ለቅናሽ ዋጋ (“የመድን ዋስትና የሌላቸው ቅናሽ”) ብቁ ይሆናሉ።

I. የቅናሽ ብቁነት፦

A. መድን ዋስትና ያልገቡ ህመምተኞች በቅድመ-ምዝገባ፣ በምዝገባ ወይም በመግቢያ ሂደት፣ ወይም በሂሳብ አከፋፈል እና በአሰባሰብ ሂደት ውስጥ ባሉ ሌሎች ቦታዎች ላይ ተለይተው ይታወቃሉ። የቤተሰብ ገቢያቸው $125,000 ዶላር ወይም ከዚያ በታች የሆነ እና ዋስትና የሌላቸውን ሁሉንም ህመምተኞች ጨምሮ፣ ነገር ግን በእነሱ ብቻ ሳይወሰን፣ መድን ዋስትና የሌላቸው እና በሕክምና አስፈላጊ አገልግሎት የሚያገኙ ህመምተኞች ከ Fairview እጅግ ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ የግል ከፋይ የኮንትራት ተመን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመድን ዋስትና ለሌላቸው የሚሰጥ የዋጋ ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ይሆናሉ።

B. በቅናሹ የማይካተቱ፦

1. አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ በሚኔሶታ ወይም በዊስኮንሲን ነዋሪ ያልሆኑ ታካሚዎች የመድን ዋስትና ለሌላቸው ለሚሰጥ የዋጋ ቅናሽ ብቁ አይደሉም።
2. ለውበት፣ ተመርጠው ለሚወሰዱ፣ ለሙከራ ወይም ለሕክምና አስፈላጊ ያልሆኑ ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያገኙ ሕመምተኞች የመድን ዋስትና ለሌላቸው ለሚሰጥ የዋጋ ቅናሽ ብቁ አይደሉም።
3. የመድን ዋስትና ለሌላቸው የሚሰጥ የዋጋ ቅናሽ የሚተገበረው በሆስፒታል እና መሰረታቸው በሆስፒታል ለሆኑ አገልግሎቶች እንዲሁም ለተመረጡ የሆስፒታል ተቀጣሪ አቅራቢ አገልግሎቶች ላይ ብቻ ነው። የነፃ ክሊኒክ አገልግሎቶችን፣ የ Fairview ካልሆኑ አቅራቢዎች የሚመጡ አገልግሎቶችን፣ በዐቃቤ ሕግ ጠቅላላ ስምምነት ያለተሸፈኑ የ Fairview አካላት የሆኑ

አገልግሎቶችን እና ሌሎች ከሆስፒታል ያልሆኑ አገልግሎቶችን የሚያገኙ ሕሙማን የመድን ዋስትና ለሌላቸው የሚሰጠውን የዋጋ ቅናሽ አያገኙም።

II. ለሚጠየቁ ክፍያዎች ቅናሽ፡-

የቅናሽ ደረጃዎች በየአመቱ መጀመሪያ በገቢ አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ይወሰናሉ። የዋጋ ቅነሳው ለ Fairview ከፍተኛ ገቢ ላላቸው የግል ከፋይ ለሆስፒታል-ተኮር አገልግሎቶች በሚሰጥ አማካይ ክፍያ መጠን ላይ የተመሠረተ ይሆናል። የጣቢያ ፋይናንስ መሪ፣ የገቢ አስተዳደር ምክትል ፕሬዝዳንት እና የገቢ ዑደት ምክትል ፕሬዝዳንት ወይም ተወካያቸው በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ግምታዊ ሁኔታዎችን በጥልቀት በመገምገም ከተቀመጡት መመሪያዎች ውጭ ውሳኔዎችን ማፅደቅ አለባቸው።

**የገንዘብ ድጋፍ**

የመድን ዋስትና ለሌላቸው ከሚሰጥ የዋጋ ቅናሽ በተጨማሪ፣ Fairview የብቃት መመዘኛዎችን ለሚያሟሉ ግለሰቦች በቅናሽ በቀረበ እንክብካቤ መልክ ብቁ ለሆኑ አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። በትዕዛዝ ሰጪ ሐኪም አስተያየት መሰረት በ Fairview እውቅና ባለው ሐኪም የታዘዙ እና በሕክምና አስፈላጊ የሆኑ የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ እና ድንገተኛ ያልሆኑ አገልግሎቶች በአጋር ድርጅት ወይም ሆስፒታሉ ካፒታል ወይም የትርፍ ወለድ በሚያገኝበት LLC በሆስፒታሉ ተቋም ውስጥ እንደሚሰጠው እንክብካቤ ሁሉ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ናቸው።

በሆስፒታል ተቋም ውስጥ የድንገተኛ አደጋ ወይም ሌላ የሕክምና አስፈላጊ እንክብካቤን የሚያቀርቡ ሠራተኛ ያልሆኑ ሶስተኛ ወገን አቅራቢዎች ከዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ጋር ከተያያዘው አባሪ ውስጥ ተዘርዝረዋል። የተያያዘው አባሪ በእነዚህ አቅራቢዎች የሚሰጠው እንክብካቤ በዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ይሸፈን እንደሆነ ያብራራል።

Fairview አማራጭ ሕክምናዎችን ወይም የአገልግሎት ቦታዎችን ለመመርመር ይችል ዘንድ የድንገተኛ ጊዜ ላልሆኑ አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄዎችን የመገምገም እና በድረጅቱ ላይ ዘላቂነት የሌለውን የገንዘብ ወጪ ጫና ሊፈጥር የሚችል ተሞክሮን ሊዘረጉ የሚችሉ የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄዎችን ለመከልከል ያለውን መብት የሚያስጠብቅ ይሆናል።

በ Fairview እንክብካቤ የሚያገኙ ታካሚዎች የመክፈል አቅማቸውን መሠረት በማድረግ ለእንክብካቤያቸው ወጪ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። የ Fairview የገንዘብ ድጋፍ በአሠሪ የተደገፈ፣ በሕዝብ ወይም በግለሰብ የተገዛ መድን ምትክ አይደለም። ለገንዘብ ድጋፉ ብቁ ለመሆን፣ ታካሚዎች የሚከተሉትን ማደረግ ይጠበቅባቸዋል፡-

- በይፋ በተደገፈ የመድን ፕሮግራም ውስጥ ለመመዝገብ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም እና ሁሉንም መረጃ ለ Fairview መስጠትን ጨምሮ ብቁ የሆኑባቸውን የመንግሥት ወይም የግል የመድን አማራጮችን ማግኘት።
- አስፈላጊ ሰነዶችን ማሳየትን ጨምሮ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ መስፈርቶችን ማክበር።

**የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት**

Fairview ለገንዘብ ድጋፍ ብቁነትን በቤተሰብ ገቢ እና ንብረት ላይ ተመስርቶ ይመለከታል። የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ቅጽ በቤተሰብ ገቢ እና ንብረቶች ማረጋገጫ ቅጽ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት። ተቀባይነት ያለው የገቢ እና የንብረቶች ማረጋገጫ ለሁሉም የቤተሰብ አዋቂ አባላት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡- በጣም የቅርብ ወር የደመወዝ ክፍያ ሂሳቦች፣ የማኅበራዊ ዋስትና፣ ሥራ አጥነትን፣ የአካል ጉዳትን እና የትዳር/የልጅ ድጋፍ ጥቅማጥቅሞችን፣ የባንክ እና የደላላ ሂሳብ መግለጫዎችን (ለገንዘብ ወይም ለአክሲዮን) እና በጣም የቅርብ ዓመቱን የግብር ክፍያ የሚያሳዩ መግለጫዎች። ለግል ተቀጣሪ አመልካቾች የገቢ መግለጫ ያስፈልጋል። ገቢ በማይኖርበት ጊዜ ገቢ አለመኖሩን የሚገልጽ መግለጫ (Declaration of No Income) ተቀባይነት ይኖረዋል።

የገቢ መመሪያዎች በሜዲኬር እና ሜዲኬይድ አገልግሎቶች ማዕከል ከታተሙት የፌዴራል የድህነት መመሪያ ማሻሻያዎች ጋር ተያይዘው ይከለሳሉ። በ Fairview የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት የገቢ መመሪያዎች እንደሚከተለው ናቸው፡-

| የቤተሰብ ገቢ እንደ የፌዴራል ድህነት መመሪያዎች % | ከጠቅላላው የቅናሽ % የተፈጸሙ ክፍያዎች (የመድን ዋስትና ለሌላቸው የሚሰጥ ቅናሽ በኋላ ባለው ቀሪ ሂሳብ ላይ) |
|---|---|
| 0-200% | 100% |
| 201%-300% | 50% |

በ Fairview የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት የንብረቶች መመሪያዎች እንደሚከተለው ናቸው፡- አንድ ቤተሰብ በባንክ ሂሳቦች፣ በአክሲዮን ንብረቶች እና በጡረታ ከ $500,000 ዶላር በላይ ጠቅላላ ንብረቶ ካለው፣ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ አይሆኑም።

Fairview የገንዘብ ድጋፍን ለታካሚዎች ለማፅደቅ ወይም ለመከልከል የትኛውንም ግምታዊ የብቃት ማረጋገጫ ሶፍትዌር አይጠቀምም። ለህክምና እርዳታ ወይም ለሚኒሶታ እንክብካቤ (በአንድነት “MA”) የሚሆን የአሁኑ ጊዜን ብቁነት ለማግኘት የተወሰነላቸው ሕመምተኞች፣ MA ተግባራዊ ከሆነበት ቀን በፊት የተከፈለ ማንኛውም የህምመተኛ ቀሪ ሂሳብ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ይሆናል።

**የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎችን ማስኬድ**

- የገንዘብ ግዴታዎችን ለማሟላት ይችሉ ዘንድ ተገቢ አማራጮችን ለመለየት እንዲረዳቸው Fairview ለታካሚዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ገንዘብ ነክ ምክር ይሰጣል። የገንዘብ ችግርን የሚያሳውቁ ታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ይሰጣቸዋል።
- ለገንዘብ እርዳታ ለማመልከት፣ አንድ ሰው የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻን መሙላት እና የቤተሰብ ገቢን እንዲሁም ንብረቶችን በተመለከተ አስፈላጊውን ሰነድ ማቅረብ አለበት (ከዚህ በታች ይመልከቱ)። የፋይናንስ እርዳታ ማመልከቻን በ 651-232-1100 ወደ HealthEast የደንበኛ አገልግሎት፣ በ 612-672-6724 ወደ Fairview Customer Service፣ ወይም በ 218-362-6624 ወደ Fairview Range Customer Service በመደወል በነፃ ማግኘት ይቻላል። እነዚህን ቁጥሮች በመደወል ማመልከቻውን በተመለከተ እርዳታ ማግኘት ይቻላል።

ከዚህ ቀደም መክፈል አለመቻልን ያልጠቆመ ታካሚ ሂሳቡን ከተቀበለ በኋላ የ HealthEast የደበኛ አገልግሎትን፣ የ Fairview የደንበኛ አገልግሎትን ወይም የ Fairview Range የደንበኛ አገልግሎትን ማነጋገር ይችላሉ፣ ወይም የፋይናንስ አማካሪ ታካሚውን ሊያነጋግር ይችላል። የደንበኛ አገልግሎት ተወካዮች ታካሚው ለተገቢ የህዝብ ድጋፍ ፕሮግራሞች ለማመልከት እና የታካሚውን የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ለማጣራት ታካሚውን ወደ ተገቢው ሠራተኛ ይልኩታል። የገንዘብ ድጋፍ ዕጩዎች የማመልከቻ ቅጽ ይሰጣቸዋል።

- ተሞልተው የተጠናቀቁ የማመልከቻ ቅጾች ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ አስተባባሪዎች ይተላለፋሉ።
- ያልተሟላ ማመልከቻ ወደ Fairview ከተመለሰ፣ የሚፈለገውን የሚገልጽ ደብዳቤ ለተጠያቂው አካል ይላካል።
- የተሟላ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ በተቀበለ በ 30 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ Fairview ስለድጋፍ ውሳኔዎቹ የጽሑፍ ማሳወቂያ ይሰጣል። ይህ ማሳወቂያ ከታካሚው የመክፈል አቅም ጋር የሚጣጣም የቅነሳ ደረጃን ያጠቃልላል። ክልከላዎች ለመከልከል ምክንያትንና ታካሚው እንደገና ግምት ውስጥ መግባት ለመቻል ማመልከት ስለሚችልበት ሂደት የተቀመጡ መመሪያዎችን ያጠቃልላሉ። እንደገና ማመልከት ሳያስፈልግ ለገንዘብ ድጋፍ የብቃት ማረጋገጫ ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆነው (በሌላ መልኩ የዚህ ፖሊሲ መስፈርቶችን ለሚያሟላ እንክብካቤ ተግባራዊ ይሆናል) ለ 6 ወራት ነው።
- የገቢ ማረጋገጫ ወይም ስለሚያባብሱ ሁኔታዎች ማብራሪያ የመሳሰሉትን ተጨማሪ መረጃዎች በፅሁፍ በ 30 ቀናት ውስጥ ለተሰየመው አረጋጋጭ አካል በማቅረብ ታካሚው ለ Fairview የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላሉ። ቀደም ሲል የተደረገው ለገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ክልከላ እንደገና ከተረጋገጠ የጽሑፍ ማሳወቂያ ለተጠያቂው አካል ይላካል። ሂሳቦቹን የመሰብሰብ ክትትል በዳግም ግምት ውስጥ የማስገባት ሂደቱ ይታገዳል።
- የገንዘብ ድጋፍ ቅናሾች ታካሚው በስምምነቱ ውሎች መሠረት ብቁ ከሆነ፣ የመድን ዋስትና ለሌላቸው ለሚሰጥ ቅናሽ ካመለከቱ በኋላ በሚቀሩት ተቀባይነት ባላቸው ቀሪ ሂሳቦች ላይ ይተገበራሉ። የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ውሳኔን ተከትሎ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ የሆነ ግለሰብ ለድንገተኛ አደጋ ወይም ለሕክምና አስፈላጊ እንክብካቤ ዋስትና ላላቸው ግለሰቦች በአጠቃላይ ከተጠየቀው መጠን (AGB) በላይ አይከፍሉም። በአጠቃላይ የተጠየቀው መጠን (AGB) ላለፈው የበጀት ዓመት ከሁሉም የንግድ እና የሜዲኬር ሂሳቦች የተገኘውን ተመላሽ ገንዘብ በመልሶ-ምልከታ ዘዴ በመጠቀም ለእያንዳንዱ ሆስፒታል ይሰላል። የ Fairview መጠን አጠቃላይ የሚከፈልበትን መቶኛ የሚገልጽ የመረጃ ወረቀትን በ 651-232-1100 ወደ HealthEast የደንበኛ አገልግሎት ፣በ 612-672-6724 ወደ Fairview የደንበኛ አገልግሎት፣ ወይም በ 218-362-6624 ወደ HealthEast Range የደንበኛ አገልግሎት በመደወል በነፃ ማግኘት ይቻላል።

የገንዘብ ድጋፍ ቅናሽ ከተደረገ በኋላ ታካሚው ለየትኛውም ቀሪ ሂሳብ ተጠያቂ ነው። ቀሪ ሂሳቡ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተከፈለ ሂሳቡ የሚከናወነው በ Fairview ሂሳብ አከፋፈል እና አሰባሰብ ፖሊሲ (Fairview Billing and Collections policy) ውስጥ በተገለፀው በተለመደው የአሰባሰብ ሂደት ሲሆን ይህም በ www.Fairview.orgላይ ይገኛል። Fairview ወኪሎቹ በምዝበራ ወይም በሕገወጥ የመሰብሰብ ልምዶች ውስጥ እንዲሠማሩ አያበረታታም ወይም አይፈቅድም።

**የገንዘብ ድጋፍ መገኘትን በማሳተም ማሳወቅ**

Fairview የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን በተለያዩ መንገዶች ማለትም በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው፣ በገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ቅጽ እና በ Fairview ድረ-ገፅ (www.Fairview.org ) ላይ ባለው ቀላል በሆነ ቋንቋ በቀረበው የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ አጠቃሎ በመሳሰሉት እና ቀላል በሆነ ቋንቋ በቀረበው የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ አጠቃሎ፣ በኤሌክትሮኒክ (በታካሚ ፈቃድ) ወይም የታተሙ ጽሑፎች በሆስፒታሎች ባሉ የሕዝብ ስፍራዎች ለታካሚዎች በማቅረብ እና በፖስታ ወይም በኢሜል (በታካሚ ፈቃድ) እና በሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ውስጥ በግልጽ በሚታዩ የሕዝብ ማሳያዎች አማካኝነት፣ እና በታካሚ የሂሳብ አከፋፈል መግለጫዎች ላይ በመሳሰሉት አማካኝነት ሕዝቡ እንዲያውቅ ያደርጋል። Fairview በ Fairview የተገለገሉትን የማህበረሰቡ አባላት ስለ ገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው በድረ-ፃቸው፣ በበራሪ መጽሔቶች እና በ Fairview ክሊኒኮች በኩል የገንዘብ ድጋፍ ብሮሹሮች ቅጂዎችን ለማህበረሰቡ አባላት በማሰራጨት ያሳውቃል።

**የበጎ አድራጎት እንክብካቤ/የገንዘብ ድጋፍ መልሶ ምደባ**

በተለመደው የአሰባሰብ ሂደት አማካይነት በተወሰነው የመክፈል አለመቻል ላይ በመመስረት Fairview ለታካሚ ሂሳብ ቀሪ ክፍያ ላለመፈለግ ሊወስን ይችላል። ክፍያ ላለመጠየቅ የወሰነነው ውሳኔ በታካሚው የገንዘብ ችግር ላይ የተመሠረተ በሚሆንበት ጊዜ፣ በስርዓቱ ዳይሬክተር ማፅደቅ እነዚህ ቀሪ ሂሳቦች በ Fairview የገንዘብ ድጋፍ ወይም የበጎ አድራጎት እንክብካቤ እንደገና ይመደባሉ።

**በመንግስት ከሚተካ ገንዘብ በላይ የሆኑ ወጪዎች**

ከሜዲኬር፣ ከሜዲኬኤድ እና ከስቴት/አካባቢያዊ የድሆች እንክብካቤ ፕሮግራሞች የተነሳ ያልተካካሱ ወጪዎች በእውነተኛ ወጪዎች እና ተተኪ ገንዘብ መካከል ባለው ከፍተኛ ልዩነት ምክንያት እንደ የማህበረሰብ ጥቅም ተካትተዋል።

**የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ፕሮግራም**

- አባሪ A ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ መመዘኛዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ይዟል
- አባሪ B መረጃ ማጭበርበርን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ይዟል።
- አባሪ C ትብብር እና የዋስትና አጠቃቀምን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ይዟል።
- አባሪ D ከበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማግለልን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ይዟል።
- አባሪ E ሌሎች የቅናሽ አማራጮችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ይዟል።
- አባሪ F ስለ ሂሳብ አከፋፈል እና አሰባሰቦች ተጨማሪ መረጃን ይዟል።

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ
# አባሪ A

**የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ፕሮግራም ብቁነት**

- ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁ የሚሆኑት የድንገተኛ ጊዜ እና በሕክምና አስፈላጊ አገልግሎቶች ብቻ ናቸው። Fairview ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁነት ዓላማ በእያንዳንዱ ግለሰብ ደረጃ አገልግሎቶች "በሕክምና አስፈላጊ ነው" የሚለውን ፍቺ ያሟሉ እንደሆነ የመወሰን መብቱን ይጠብቃል።
- ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁ ለመሆን፣ አንድ ታካሚ የገቢ እና የንብረት መመሪያዎችን እንደሚከተለው ማሟላት አለበት፦
  1. የገቢ ደረጃ፦ የታካሚው የተጠቃለለ ዓመታዊ የቤተሰብ ገቢ የፌዴራል የድህነት ደረጃን (FPL) 300% ወይም ከዚያ በታች መሆን አለበት።

**የገቢ ገደቦች በቤተሰብ መጠን**

| የቤተሰብ መጠን | ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ (200% FPL (የፌዴራል የድህነት ደረጃ)) | ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ (300% FPL (የፌዴራል የድህነት ደረጃ)) |
|---|---|---|
| 1 | $25,760 | $38,640 |
| 2 | $34,840 | $52,260 |
| 3 | $43,920 | $65,880 |
| 4 | $53,000 | $79,500 |
| 5 | $62,080 | $93,120 |

  2. በ Fairview የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት የንብረቶች መመሪያዎች እንደሚከተለው ናቸው፦ አንድ ቤተሰብ በባንክ ሂሳቦች፣ በአክሲዮን ንብረቶች እና በጡረታ ከ $500,000 ዶላር በላይ ጠቅላላ ንብረቶ ካለው፣ ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ አይሆኑም።
  3. ገቢን እና nbretocn ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን ሰነድ የተመለከቱ ዝርዝሮች በ "የትግበራ ሂደት" ስር ከዚህ በታች ይገኛሉ።

- የገቢ ስሌት፦
  - ለአዋቂዎች በበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻ ላይ "ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ" የሚለው ሐረግ የአመልካቹን እና የአመልካቹን የትዳር አጋር አመታዊ ጠቅላላ ገቢን ከሁሉም ምንጮች ያመለክታል። አመልካቹ ለአካለ መጠን ያልደረሰ/ች ከሆነ፣ "ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ" የሚለው ሐረግ የአመልካቹን/ቿን ወላጅ(ጆች) እና/ወይም ሕጋዊ አሳዳጊን አጠቃላይ ገቢ ያመለክታል። በበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው "ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ" አኃዝ ከ 12 ወራት በላይ የተመዘገበውን

ዓመታዊ ገቢ ያመለክታል። የአሁኑን ዓመታዊ ገቢን ማስላትን ለማገዝ ቢያንስ አንድ ያለፈው ወር የገቢ ማረጋገጫ ይጠየቃል። ያለፈው ወር የገቢ ማረጋገጫ የማይገኝ ከሆነ፣ ታካሚው የሰነዱን ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ በጣም የቅርብ ጊዜውን መጠን ልታቀርቡ ይችላሉ። ታካሚው/ዋ በፌርቪው ከተሰጠው/ከተሰጣት እንክብካቤ ጋር የተዛመደ የሶስተኛ ወገን የገንዘብ ዕርዳታ ከተቀበሉ እንደዚህ ዓይነቶቹ የገንዘብ ድጋፎች በታካሚው ለ Fairview ያለውን ዕዳ ለማሟላት ጥቅም ላይ ለመዋል ስለሚጠበቁ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ሊሰጥ አይችልም። ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ የሚያመለክት ታካሚ የቤተሰብን መጠን፣ ገቢን እና ንብረቶችን ለመወሰን በታካሚው ቤተሰብ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ቁጥር እንደሚከተለው ሪፖርት ያደርጋሉ፡-

አዋቂዎች፡- በአዋቂ አመልካች ቤተሰብ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ብዛት ሲያሰላ፣ Fairview አመልካቹን፣ የአመልካቹን የትዳር አጋር እና ማንኛውንም ሕጋዊ ጥገኞችን ያካትታል።

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች:- በአካለ መጠን ያልደረሰ አመልካች ቤተሰብ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ቁጥር በማስላት፣ Fairview አመልካቹ፣ የአመልካቹን/ቿን አባት/አሳዳጊ፣ እናት/አሳዳጊን፣ እና የአባቱን ፣ የእናቱን ወይም የአካለ መጠን ያልደረሰውን ማንኛውንም ጥገኞች ያካትታል።

ሕጋዊ ሞግዚትነት/ጠባቂነት በሕጋዊ የሕግ ሰነዶች ካልተረጋገጠ በስተቀር፣ ከአዋቂ ልጃቸው ጋር በቤት ውስጥ የሚኖሩ ወላጆች በዚያ ልጅ የቤተሰብ መጠን ወይም ገቢ ውስጥ አይደመሩም።

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ
# አባሪ B

**መረጃ ማጭበርበር**

- መረጃ ማጭበርበር፦
    - የገቢ መረጃን ማጭበርበር ወይም በማመልከቻው ሂደት ከ Fairview ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ አለመሆን የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻን መከልከልን ያስከትላል። አንድ አመልካች የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ከተሰጠው በኋላ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻ ቁሳቁስ አቅርቦቱ እውነት አለመሆኑን Fairview ከተረዳ፣ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማመልከቻ እና የተሰጠው ማንኛውም የበጎ አድራጎት እንክብካቤ በ Fairview ብቸኛ ውሳኔ ሊነሳ ይችላል።

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ
# አባሪ C

**የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ፕሮግራም ትብብር እና የመድን ዋስትና አጠቃቀም**

የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ፕሮግራም ለግል ኃላፊነት መውሰድ ምትክ ስላልሆነ፣ በፕሮግራሙ በኩል የገንዘብ ድጋፍ የሚሹ ሰዎች ብቁነትን ለመወሰን ከ Fairview ሂደቶች ጋር መተባበር እና በግለሰባዊ ችሎታቸው መጠን ለአገልግሎቶቹ ዋጋ አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። Fairview ቀጣይ የመከላከል የጤና አገልግሎቶችን ተደራሽነት ለማረጋገጥ እና የግል ንብረቶቻቸውን ለመጠበቅ ይችሉ ዘንድ የገንዘብ አቅም ያላቸውን ግለሰቦች የጤና መድን እንዲገዙ ያበረታታል። ብቁ ከሆኑ ሁሉም ታካሚዎች ምርመራ የሚደረግባቸው ሲሆን እንደ ተባባሪ ለመቆጠር በተመጣጣኝ እንክብካቤ ሕግ (ACA) ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት በ MNsure ለሜዲኬይድ፣ በ MinnesotaCare፣ ብቃት ባለው የጤና ዕቅድ (Qualified Health Plan) ወይም በሌላ ተቀባይነት ባለው የጤና እንክብካቤ ሽፋን በኩል ማመልከት ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

- አንድ ታካሚ ለሶስተኛ ወገን የገንዘብ ምንጭ ብቁ ከሆነ እና ከታካሚው ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ሁኔታዎች ምክንያት ካልተባበረ፣ ታካሚው የማብራሪያ ደብዳቤ እንዲያቀርብ ይገደዳል። ደብዳቤው በ Fairview አስተዳደር ይገመገማል።
- አንድ ታካሚ የሶስተኛ ወገን ከፋይ ካለው እና የከፋይን መረጃን በወቅቱ ለ Fairview ካላቀረበ ታካሚው ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ወይም ለሌላ ለማንኛውም የፌርቪው የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም ብቁ አይሆንም።
- በአጠቃላይ፣ አንድ ታካሚ በአሠሪው በኩል መድን ካለ ላለመውሰድ ከመረጠ፣ ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁ ላይሆን ይችላል። በ MNsure በኩል ለሕክምና እርዳታ፣ MinnesotaCare ወይም ብቃት ላለው የጤና እቅድ (Qualified Health Plan) ማመልከት አለባቸው።
- አንድ ታካሚ ለተለየ አሠራር ወይም የአገልግሎት ቀን እመድን ሂሳቡን ላለመክፈል ከመረጠ ለዚያ የመጣበት ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁ አይሆንም።

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ
# አባሪ D

### የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ፕሮግራም የማያካትታቸው፡-

የ Fairview በጎ አድራጎት እንክብካቤ ፕሮግራሞች እና ሌሎች የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ዕቅዶች የሚከተሉትን አይሸፍኑም፡-

- የበጎ አድራጎት እንክብካቤ የማመልከቻ ሂደትን የማያከብሩ ታካሚዎች የበጎ አድራጎት እንክብካቤን ሊከለከሉ ይችላሉ።
- አመልካች ከሚያስገባው የሶስተኛ ወገን የሀብታት ማመልከቻ ወይም መሰብሰብን በተመለከተ መተባበር ካልቻለ እና የታካሚ ሂሳብ ከመድን ኩባንያ ጋር በመጠባበቅ ላይ ከሆነ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ይከለከላል።
- የ Fairview ካልሆኑ አቅራቢዎች፣ በዚህ ፖሊሲ ያልተሸፈኑ የ Fairview አቅራቢዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች።
- በ Fairview Express ክሊኒኮች የተከናወኑ አገልግሎቶች።
- ከመጓጓዣ፣ ወይም ከግል የኑሮ ወጪዎች ጋር የተዛመዱ ወጪዎች
- ንቅለ ተከላው (ትራንስፕላንት) ከተደረገ ከአንድ ዓመት በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥ ለንቅለ ተከላ ታካሚዎች የተከፈሉ ተዛማጅ ክፍያዎች ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ቅናሽ ብቁ አይደሉም። ለእነዚህ ለውጦች ማስተካከያ የሚሆን ማንኛውም ምክረ-ሃሳብ በፋይናንስ ልዩ ሂደት (Financial Exception process) ውስጥ ማለፍ አለበት።
- የዩናይትድ ስቴትስ ያልሆኑ ዜጎች፣ ቋሚ ያልሆኑ ነዋሪዎች፣ ወይም ከአሜሪካ ውጪ የሚኖሩ የዩናይትድ ስቴትስ ዜጎች ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁ የማይሆኑ ሲሆን ይህም በቪዛ ላይ ያሉ ታካሚዎችን እና ዓለም አቀፍ ተማሪዎችን ያጠቃልላል። ይህ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚኖሩ ሰነድ አልባ ግለሰቦችን እና ቋሚ ያልሆኑ ነዋሪዎችን አያካትትም። የአሜሪካ ቋሚ ነዋሪዎች/ግሪን ካርድ
- የ Fairview ከሆስፒታል ወጪ አገልግሎት ሰጪ ክሊኒኮች (Free Standing Clinics) ከስቴቱ ውጭ በሚሰጥ የሕክምና እርዳታ አይሳተፉም። ስለዚህ፣ ከሆስፒታል ወጪ አገልግሎት ሰጪ ክሊኒኮች ክፍያዎች ያሏቸውና ከስቴት ውጭ የሜዲኬይድ ሽፋን ያላቸው ታካሚዎች ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁ አይደሉም።
- እንደ የእንክብካቤ መስፈርት ካልተቆጠረ በስተቀር፣ አገልግሎቶች በአብዛኛዎቹ የመድን አቅራቢዎች እንዳልተሸፈኑ ይቆጠራሉ።
- ስራው የችርቻሮ ባህሪ ስላለው፣ የ Fairview የቤት ህክምና መሣሪያዎች እና የ Fairview ኦርቶቲክስ እና ፕሮስቴቲክስ (ሰው ሰራሽ የእግርና የእጅ ክፍሎች እና አመቻቺ ማሣሪያዎች) በዚህ ፖሊሲ ስር አይሸፈኑም።
- የ Fairview የቤት ውስጥ እንክብካቤ (Homecare) እና የፌርቪው ፋርማሲ የራሳቸው የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ፖሊሲዎች ስላሏቸው በዚህ ፖሊሲ ስር አይሸፈኑም።
- ከ Fairview ጋር ቁርኝት ያላቸው ቦታዎች፣ ሁሉንም ባያካትትም፣ እንደ የ Fairview ማፕል ግሮቭ አምቡላቶሪ የቀዶ ሕክምና ማዕከል፣ ክሮስታውን የቀዶ ጥገና ማዕከል እና ግሪንቪው አልዛይመርስ የመሳሰሉት በተናጠል ያሉ የኮርፖሬት አካላት ሲሆኑ ለዚህ ፖሊሲ የማይገዙ ናቸው።
- የ Fairview ባልሆኑ አካላት የሚሰጡ የሙያ አገልግሎቶች በዚህ ፕሮግራም ስር አይሸፈኑም።

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ
# አባሪ E

**የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ፕሮግራም:- ሌሎች የቅናሽ አማራጮች**

- ገንዘብ ነክ ልዩ ሁኔታዎች (Financial Exceptions)
    - የታካሚው/ዋን የመክፈል ችሎታ ለመወሰን የተሰየመ የፌርቪው ማኔጅመንት ሁሉንም ልዩ ሁኔታዎች ይገመግማል። የሚከፍሉት የገንዘብ አቅም ለሌላቸው ታካሚዎች የሚመለከታቸው የተለዩ ጉዳዮች ብቻ ተሠርተው እንደ በጎ አድራጎት እንክብካቤ ሪፖርት ይደረጋሉ። በስቴት እና በፌዴራል መመሪያዎች በተገለጸው መሠረት ሁሉም ሌሎች ጉዳዮች እንደ አስተዳደራዊ ማስተካከያዎች ተደርገው ሪፖርት ይደረጋሉ እንጂ እንደ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ወይም የከፋ ዕዳ አይገለጹም። ከፌድራል የድህነት ደረጃ (FPL) መመሪያዎች ያለፈ አመልካች ሆኖ ካለፈው ዓመት ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢ የሚበልጥ ጠቅላላ የህክምና ዕዳ ያለው አመልካች በገንዘብ ነክ ልዩ ጉዳዮች አማካኝነት ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ለማመልከት ሊፈቀድለት ይችላል።
- ከፍተኛ አጋሮች:-
    - የፌርቪው ከፍተኛ አጋሮች በ Fairview እና በከፍተኛ የማህበረሰብ አገልግሎቶች መካከል ያለ ሽርክና ነው። Fairview የሆስፒታል እና የክሊኒክ የጋራ መድንዎችን እና ተቀናሽ ሂሳቦችን ለመተው ተስማምቷል። በሜዲኬር ላልተሸፈኑ ለማናቸውም ነገሮች፣ ለምሳሌ ወደ ቤት የሚወስዱ መድኃኒቶች ተጠያቂዎች መሆናቸውን የዚህ ፕሮግራም አባላት ይረዳሉ። የበጎ አድራጎት እንክብካቤ አስተባባሪ ሂሳቦችን ያስተካክላል። ከሜዲኬር የተሰበሰቡ መጠኖች ከበጎ አድራጎት እንክብካቤ ማስተካከያ ጋር ይካካሳሉ።
    - የምዝገባ ማመልከቻዎች
        - ሁሉም ማመልከቻዎች የሚላኩት ወደ ከፍተኛ የማህበረሰብ አገልግሎቶች ወይም ወጣ ብለው ወደሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሲሆን ሂደታቸውም የሚከናወነው በእነዚሁ አካላት ነው። ታካሚዎች ለሜትሮ አካባቢ በ 952-767-0665 በመደወል ወይም በበይነ መረብ www.seniorcommunity.org ን በመጎብኘት ወይም ለሬንጅ በ 1-800-662-5711 or በመደወል ወይም በኢንተርኔት www.aeoa.org/senior-services ን በመጎብኘት ማመልከቻ ወይም ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ ይችላሉ።
    - የብቁነት መስፈርቶች
        - ታካሚው በሜዲኬር ክፍሎች A እና B መመዝገብ አለበት/አለባት ፤ በመተካት ዕቅድ (replacement plan) ላይ ያለ መሆን የለበትም።
        - የሜዲኬር ማሟያ ሊኖረው አይችልም።

- Retro የበጎ አድራጎት እንክብካቤ/ለህክምና ድሃ ለሆኑ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ
    - አንድ ታካሚ የአሁኑ ጊዜ ኤምኤ (MA) ወይም ሚኔሶታ ኬር ካለው/ካላት እና ሁሉም የቀደሙት የአገልግሎት ቀናት በኤምኤ (MA)/MinnesotaCare ካልተሸፈኑ፣ ከኤምኤ (MA) ማጽደቂያ ቀን በፊት የተከሰተ ማንኛውም ሂሳብ ለበጎ አድራጎት እንክብካቤ ብቁ ሊሆን ይችላል።
- የመድን ሽፋን ለሌላቸው የሚሰጥ ቅናሽ
    - በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ስር ከሚገኙት ፕሮግራሞች በተጨማሪ፣ የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ቅናሽ ከመተግበሩ በፊት፣ የመድን ሽፋን የሌላቸው የሚኔሶታ እና የዊስኮንሲን ነዋሪዎች የሆስፒታሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት ይችሉ ዘንድ የመድን ሽፋን ለሌላቸው የሚሰጥ ቅናሽ ብቁ ይሆናሉ። ይህ ቅናሽ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የአሰባሰብ ደረጃዎች ስምምነት ላይ የተመሠረተ እና የበጎ አድራጎት እንክብካቤ ፕሮግራም ያልሆነ ነው።

# የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ
# አባሪ F

**የሂሳብ አከፋፈል እና አሰባሰቦች**

- Fairview በድረ-ገጹ [www.Fairview.org](http://www.Fairview.org) በኩል፣ ወይም በ 612-672-6724 ወደ Range የደንበኛ አገልግሎት፣ ወይም በ 1-888-702-4073 በነፃ በመደወል፣ ወይም በ 651-232-1100 ወደ HealthEast የደንበኛ አገልግሎት፣ ወይም በ 1-866-770-6411 በነፃ በመደወል፣ ወይም በ 218-362-6624 ወደ Fairview Range የደንበኛ አገልግሎት፣ ወይም በ1-877-390-6624 በነፃ በመደወል የሚገኝ የተለየ የሂሳብ አከፋፈል እና የአሰባሰብ ፖሊሲ አለው። ይህ ፖሊሲ ስለሚከተሉት የበለጠ ልዩ መረጃን ያካትታል፡-
  - የሂሳብ አከፋፈል ሂደት፡- Fairview በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሂሳብ አከፋፈል መግለጫዎችን የሚያወጣ ሲሆን በሂሳብ ላይ ያልተለመዱ የመሰብሰብ እርምጃዎችን ከመጀመሩ በፊት ከመጀመሪያው የድህረ-ጉብኝት ሂሳብ አንስቶ ቢያንስ 120 ቀናት ይሰጣል።
  - ለሂሳቦች መፍትሔ መስጠት፡- Fairview ብቁ የሆነ መድን ወይም የሕክምና ዕርዳታን፣ የክፍያ ዝግጅቶችን፣ የበጎ አድራጎት እንክብካቤን ወይም ሌሎች መንገዶችን በመለየት ክፍት ሂሳቦችን በተለያዩ አማራጮች ለመፍታት ቢያንስ 240 ቀናት ይሰጣል።
  - የአሰባሰብ እርምጃዎች፡- ክፍያ ባለተፈጸመበት ሁኔታ፣ Fairview ሂሳቦችን እንዲከታተሏቸው ለሰብሳቢ ኤጀንሲዎች እና/ወይም ሕጋዊ የአሰባሰብ ድርጅቶች ሊልክ ይችላል። በሂሳብ ላይ ያልተለመዱ እርምጃዎች ከመጀመራቸው በፊት Fairview ቢያንስ ከ 30 ቀናት በፊት የታካሚ ማሳወቂያ ይሰጣል።

**የአቅራቢ ዝርዝር**

Fairview በ Fairview ሆስፒታል ተቋም ውስጥ ለታካሚዎች የድንገተኛ እና የህክምና አስፈላጊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የሁሉም የአቅራቢ ቡድኖች ዝርዝር አለው። ዝርዝሩ የትኞቹ አቅራቢዎች በ Fairview የፋይናንስ ድጋፍ ፖሊሲ የተሸፈኑ እንደሆነ እና የትኞቹ ደግሞ ያልተሸፈኑ መሆናቸውን ይለያል (የተያያዘውን ማስፈንጠሪያ ይመልከቱ)። [https://www.fairview.org/search/doctors](https://www.fairview.org/search/doctors)

ወይም [https://www.healtheast.org/images/stories/billing/covered_providers.pdf](https://www.healtheast.org/images/stories/billing/covered_providers.pdf)

**የድርጅት ትግበራ፡-**

የ Fairview Lakes የሕክምና ማዕከል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
የ Fairview Northland የሕክምና ማዕከል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
የ Fairview Range የሕክምና ማዕከል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
የ Fairview Ridges ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
የ Fairview Southdale ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
Grand Itasca ክሊኒክ እና ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
HealthEast ሴንት ጆንስ ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
HealthEast ሴንት ጆሴፍ ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
HealthEast Woodwinds ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
HealthEast Bethesda ሆስፒታል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
HealthEast ክሊኒኮች እና ሌሎች ከግብር ነፃ የሆኑ ድርጅቶች ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
የሚኒሶታ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ማዕከል ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።
የ Fairview ሜዲካል ግሩፕ ይህንን ፖሊሲ በስራ ላይ አውሏል።

**የፖሊሲው ባለቤት፡-**

የገቢ ዑደት ምክትል ፕሬዝዳንት

**ያጸደቀው፡-**

የ Fairview የዳይሬክተሮች ቦርድ

**ቀን(ናት)**

**ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን:-** 2-18-07፣ በቦርድ የፀደቀ
**የተተኩ –** የማህበረሰብ እንክብካቤ ክፍል ቦርድ በ12-16-04 ለታካሚ አገልግሎቶች የገንዘብ ዝግጅቶችን አጽድቋል

**የተሻሻለበት ቀን:-** 2/1/15፤ 12/1/15፤ 12/29/2015፤ 1/29/2016፣ 7/24/2017፣6/20/19፣2/10/20፣ 2/1/21

**የተከለሰበት ቀን:-** የ Fairview ቦርድ በድጋሚ አይቶ እንደገና አጽድቋል፡- 4/16/15፣ 6/17/16፣ 8/17/17፣ 11/5/19፣ 8/5/21

**ክለሳው ተግባራዊ የሆነበት ቀን፡-** 6/1/15 ፣ 6/17/16 ፣ 11/1/17